የልደት መዝሙራት

1) ስብሃት ለእግዚአብሔር በሰማያት
   ወሰላም በምድር ሥምረቱ ለሰብእ ሃሌ ሉያ(2)
   ሃሌ ሉያ(3) አሜን ሃሌ ሉያ(2)
2) በቤተልሔም ተወልደ(2) አማኑኤል
   እም ዘርአ ዳዊት(5) ተወልደ አማኑኤል
3) በጎል ሰከበ በአጽርቅት ተጠብለለ
   ቤዛ ኩሉ ዓለም(2) ዮም ተወልደ

4. **እሰይ ተወለደ**
   እሰይ ተወለደ የዓለም መድኃኒት (3)
   ይኸው ተወለደ የዓለም መድኃኒት(3)
   ትንቢት ተናገሩ ነቢያት በሙሉ(3)
   አምላክ ቀዳማዊ ይወርዳል እያሉ(3)
   አዝማች
   ትንቢት ተናገሩ ነቢያቱ ሁሉ(3)
   የእስራኤል ንጉሥ ይወርዳል እያሉ(3)
   አዝማች
   ሰብአ ሰገል መጡ ሊሰግዱ በሙሉ(3)
   የእስራኤል ንጉሥ ተወልዶዋል እያሉ(3)
   አዝማች
   ሰብአ ሰግል መጡ እጅ መንሻ ይዘው(3)
   ወርቅ እጣን ከርቤውን ገበሩለት ሰግደው (3)
   አዝማች
   ሕጻናት እንሂድ ከልደቱ ቤት(3)
   ውሃ ሆኖዋል እና ማርና ወተት(3)

5. ስብሃት ለእግዚአብሔር በሰማያት
   ወሰላም በምድር(3) ሰምረቱ ሰብእ አዝማች(2)

   በሃጢአት የወደቀ አዳምን ሊያነሳ
   አምላክ ተወለደ በጎለ እንስሳ

ሕዝቡ ሲኖር ሳለ ጨለማ ዉጠት
አየ ብርሃንን በአማላኩ ልደት
በዳዊት ከተማ በከብቶች በረት
ይኸው ተወለደ የአለም መድኃኒት
ጠፍቶ እንዳይቀርበት ርቆ ከመንጋ
አምላክ ተወለደ አዳምን ፍለጋ
ሰግደው ገበሩለት ወርቅ እጥን ከርቤን
ሰው ለሆነው አምላክ አዳምን ሊያድን
ምነው ባደረገን እኛም እንደ እረኞች
እንደ ሰብአ እንደ ጥበብ ሰዎች

6. እንደ ዮሴፍ ወይ እንደ ሰሎሜ <u>በሆን</u>(2)
ኢየሩሳሌም(3) በሆን አምላክ ሲወለድ ባየን

7) ዮም ሰማያዊ በጎል ሰከብ ለዘተወልደ እምቅድስት ድንግል
ርእይዎ ኖሎት(2) አእኩትዎ መላእክት(2)

8) <u>ዛሬ ተወለደ</u>
ዛሬ ተወለደ የአለም ቤዛ (2)
ወገኖቹን በደሙ ሊገዛ(2)
የጠፋውን አዳም ለመፈለግ ሸቶ
ዘጠና ዘጠኙን መላእክት ትቶ
ወልደ አብ ክርስቶስ ከሰማይ ወረደ
ረቂቅ መለኮት ሥጋን ተዋሃደ (2)

ተጠቅልሎ በጨርቅ በበረት ተጥሎ
አምላካችን ታየ ቅጠል ተከልሎ
ተወልዶ ተገኘ በትሁት ስብዕና
እጅግ ያስገርማል የአምላክ ትህትና(2)
በኤፍራታ ክፍል በቤትልሔም
አምላክ ተወለደ መድሃኔዓለም
ካህናት ሁልጊዜ እንቺን ያነሳሉ
ቤተልሔም ሆይ ተፈስሒ እያሉ(2)

ጌታ ተወለደ በዳዊት ከተማ
አለምን ለማውጣት ከሃጢያት ጨለማ
አምላክ መወለዱን ዝቅ ብሎ ከክብሩ
ስለእኛ ነውና እንዘምር ዘምሩ (2)

9. <u>የምሥራች</u>
የምሥራች ደስ ይበለን(2)
የዓለም መድሃኒት ተወለደልን
ምሥራች ደስ ይበለን
አዝማች
ንጉስ ሄሮድስ ይህን ሲሰማ(2)
ፈልጋችሁ አምጡት በቀን በጨለማ(2)
አዝማች
ሰብአ ሰገል እንደታዘዙት(2)
በኮከብ ተመርተው ህጻኑን አገኙት(2)
አዝማች
ሠገዱለት ከመሬት ወድቀው
ወርቅና እጥኑን በረከቱን ሰጥተው
አዝማች

10. መጽአ ከመይቤዞ ለዓለም
የሀበነ ሰላመ ጋዳ ያበወኡ ቁርባነ

11. እስይ የምሰራች ጌታ ተወለደ መድኃኔዓለም
ለዓለም(2) ለዓለም ብርሃን(2)

12. የጥበብ ስዎች መጡ

የጥበብ ስዎች መጡ(2) ስምተውት በዜና
እያበራላቸው ኮከቡ እንደፋና(2)
ሰብአ ሰገል መጡ ሊሰግዱ በሙሉ
የእሰራኤል ንጉሰ ወዴት አለ እያሉ

አዝማች - የጥበብ ስዎች
እጅ መንሻውን ስጡ እንደየሥርዓቱ
እጣኑን ለክህነት ወርቁን ለመንግስቱ

አዝማች
መድህን ተወለደ በቤተለሔም
ኩነኔን አጥፍቶ ጽድቅን ሊያወርስን

አዝማች
አንቺ ቤተለሔም በጣም ደስ ይበልሽ
ለአምላክ ወገኖች መመኪያቸው የሆንሽ

13.የዓለም መድኃኒት

የዓለም መድኃኒት የተወለደብሽ
አንቺ ቤተልሔም የተቀደሰሽ ነሽ

የአማልክት አምላክ ንጉሠ ነገሥት
ኃያላን በሙሉ የሚሰግዱለት
በጨርቅ ተጠቅልሎ ተኛ ከበረት(2)

አዝማች የዓለም ...

አዋቂዎች ሁሉ በቅን ሀሳባቸው
ወደ አንቺ ተጉዋዙ ኮከብ ቢመራቸው(2)

አዝማች

ለተከታይ ትውልድ ምሳሌ ለመሆን
ሰግደው ገበሩለት ወርቅ ዕጣን ከርቤን(2)

አዝማች

የሚያድለው ጌታ እወቀት ለሕጻናት
የሚመሰገነው በአፈ መላእክት
ከእንስሳት ጋራ አደረ በበረት

አዝማች

በሥጋ ተገለጠ ረቂቅ ምሥጢሩ
ሰውና መላእክት በአንድ ላይ ዘመሩ(2)